የ ቅ ዱ ሳ ት መ ጻ ሕ ፍ ት አ መ ጣ ጥ ታ ሪ ክ

(በጎሩይ ጽጌ ተዘጋጀ 1971-1979 ዓ.ም.)

መጽሐፍ ቅዱስ ምንድነው?

መጽሐፍ ቅዱስ የሚለው ቃል ከግሪኩ ቢብልያ ማለትም "መጻሕፍት" ከሚለው ቃል የተገኘ ነው። ይህ ስም ቀስ በቀስ እየተለመደ መጥቶ በተለይ ከ2ኛው መቶ ዓመት ወዲህ ቋሚ የቅዱሳት መጻሕፍት መጠሪያ ሆነ። (1 መቃቢያን 12፡9)

"መጽሐፍ ቅዱስ" ስንል በእግዚአብሔር ዕቅድ ትውልድ ሁሉ እንዲመራበት በመጽሐፍ ስፍሮ የተላለፍልን የእግዚአብሔር ቃል ማለታችን ነው። (ሮሜ 14፡4፤ 1 ቆሮ 10፡6-11፤ 1 ጢሞ 3፡14-15)

በዚህ ዓይነት ብሉይና ሐዲስ ተብለው የሚጠሩትን ቅዱሳት መጻሕፍት ባንድ ላይ "መጽሐፍ ቅዱስ" እንላቸዋለን"። በሌሎት የሃይማኖት ክፍሎችም "ቅዱሳት" ተብለው የሚጠሩ መጻሕፍት አሉ። ለክርስቲያኖች ግን አንድ ብቻ እውነተኛ "ቅዱስ" የሕይወት መጽሐፍ አለ። እርግጥ ነው መጽሐፍ ቅዱስ "የተሳሳተ መጽሐፍ ነው" በማለት በኢአማንያን ብዙ ነቀፋና ጥርጥር የተሰነዘረበት እስከ ዛሬም የሚሰነዘርበት መጽሐፍ ነው። ይሁንና መጽሐፍ ቅዱስ እውነኛና ትክክለኛ መጽሐፍ ለመሆኑ ዘመናዊ ሳይንስ እንኳ እየመሰከረለት ነው። በተለይም በየጊዜው የሚገኙ የአርኪኦሎጂ ታሪካዊ ማስረጃዎች ዋና ምስክር ሆነዋል።

መጽሐፍ ቅዱስ በእግዚአብሔር መንፈስ የተጻፈ ሕያው ቃል ነው፤ (ኤር 35፡2፤ ሕዝ 1፡3፤ 2ጢሞ 3፡16-17፤ 2 ጴጥ 1፡21) በዚህ ዓይነት ምንም ጸሐፊዎቹ ከሰው ያልተለዩ ባይሆንም መንፈስ ቅዱስ በሰጣቸው መገለጥ እየተመሩ መጻሕፍትን ጽፈዋል።

የጻሐፊዎቹ ብዛት የብሉይ ኪዳን 40፤ የአዲስ ኪዳን 8 ያህል ነው። መጻሕፍቱ የተጻፉበት ዘመን ብሉይ ኪዳን ከ1400-400 ዓ.ዓ. ሲሆን አዲስ ኪዳን ከ45-96 ዓ.ም. ባሉት ዓመታት ውስጥ ነው።

ይህን በሚያህል የተራራቀ ዘመን መካከል በማይተዋወቁ ሰዎች ተጽፈው አንድ ዓላማና መልእክት መያዛቸው መጽሐፍ ቅዱስን እውነተኛ ከሚያደርጉት ማስረጃዎች አንዱ ነው።

ሌሎች በርካታ የሃይማኖት መጻሕፍት አሉ፤ ይሁንና እንደ መጽሐፍ ቅዱስ የእውነት ቅደም ተከተል፣ የታሪክ አድገት፣ ወይም ፕላን የላቸውም። መጽሐፍ ቅዱስ ሥልጣን ያለው የሚሠራ ሕያው ቃል ነው። እግዚአብሄር በቃሉ የሚናገረውን ይፈጽማል፤ በፍጥረት ታሪክ እንደምናየው "ይሁን" አለ ሆነም። (መዝ 3፡6-9፤ ኢሳ 55፡11፤ ዕብ 4፡11) ስለዚህ ነው በቃሉ ለሕዝቡ የሰጣቸው ተስፋዎች ሁሉ ይሆናሉ ብለን የምናምነው።

ቅዱሳት መጻሕፍት ወደ እኛ እንዴት ደረሱ?

ይህ ጽሑፍ የተዘጋጀው ቅዱሳት መጻሕፍትን ማን ጻፋቸው? እንዴት ተጻፉ? መቼ? የት? ለምን? የሚሉትን የቲኦሎጂ ጥያቄዎች ለመመለስ ሳይሆን በመሠረታዊዎቹ ቋንቋዎች ከተጻፉ በኋላ ይህን ሁሉ ዘመን እንዴት ኖሩ? ወደ እኛስ እንዴት ደረሱ? የሚሉትን ታሪካዊ ጥያቄዎች ለመመለስ ያህል ነው። በሌላም በኩል የቅዱሳት መጻሕፍት አመጣጥ በጣም ሰፊ ታሪክ በመሆኑ በዚህ አጭር ጽሑፍ በዝርዝር መግለጽ የማይቻል በመሆኑ ለመግቢያ ያህል ብቻ ባጭር ባጭሩ ተጠቅሷል።

የአይሁድ መጻሕፍት ዝርዝር (ካነን)
አይሁዶች 39ኙን የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በሦስት ዋና ዋና መደብ ይከፍሏቸዋል። (ሉቃ 24፡44) ጠቅላላ የመጻሕፍቱ ዝርዝር 24 ነው፤ ምክንያቱም እኛ በሁለት ክፍል የምናውቃቸውና የደቂቀ ነቢያት መጻሕፍት (ከሆሴዕ-ሚልክያስ) ሰለሚታጠፉ ነው። ጠቅላላ ዝርዝሩ እነሆ፡

1. ብሔረ ኦሪት - ከዘፍጥረት እሰከ ዘዳግም
2. ነቢያት - ሀ. የቀድሞ ነቢያት - ኢያሱ፤ መሣፍንት፤ ሳሙኤል፤ ነገሰት
   ለ. የኋለኞች ነቢያት - ኢሳያስ፤ ኤርሚያስ፤ ሕዝቅኤል፤ ደቂቀ ነቢያት
3. ጽሑፎች - ሀ. መዝሙረ ዳዊት፤ ኢዮብ፤ ምሳሌ፤ ዜና መዋዕል፤ ዕዝራና ነህምያ
   ለ. ጥቅሎች - ሩት፤ መኃልየ መኃልይ፤ ሰቆቃው ኤርሚያስ፤ መክብብ፤ አስቴር ዳንኤል።

የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ዝርዝር (ካነን)
ካነን "እውነተኛና ትክክለኛ ናቸው" በማለት ቤተ ክርስቲያን እንደ እግዚአብሔር ቃል የተቀበለቻቸው የቅዱሳት መጻሕፍት ዝርዝር ነው።

ሰለዚህ ቅዱሳት መጻሕፍት ትክክለኛ ናቸው ተብለው በመመረጥ ተቀባይነት አግኝተው ባንድ ጥራዝ የተወሰኑት መጻሕፍት በእንግሊዘኛ ካነን ይባላሉ። ካነን ማለት በግሪክኛ መለኪያ፤ ዘንግ (መመዘኛ) ማለት ነው። እንደምናውቀው የአይሁድ መጽሐፍት እሰከ ዛሬ ብሉይ ኪዳን ብቻ ነው። እነርሱ የተቀበሏቸው መጻሕፍት 39 ብቻ እንደ ሆኑ የታወቀው ታሪክ ጻሕፊያቸው ዮሲፈስ ይገልጻል።

አላይ እንደተገለጠው በአይሁድ ካነን 39ኙ የብሉይ ኪዳን መጻህፍት ብቻ ይገኛሉ። ካነናቸውም የተወሰነው ክክርስቶስ ልደት በፊት ሲሆን፤ በ400ዎቹ የዝምታ ዓመቃት ውስጥ እንደተጻፉ የሚገመቱ ዛሬ "አዋልድ" የምንላቸው መጻሕፍት መባዛትና የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት መፈጠር ሰላሳሰባቸው እንደገና በ90 ዓ.ም. ገደማ ጉባኤ አድርገው የቀድሞዎቹን አጽንተው አዋልዱን አንዳወገዙ ይተረካል። ይሁንና አዋልዱን በካነናቸው የጨመሩ በሰደት የሚኖሩ የነበሩ የአሌክሳንደሪያዎቹ አይሁድ አንጂ ዋናቹ አይሁድ ተቀብለዋቸው አያውቁም። በዚህም መሠረት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት 39፤ የአዲስ ኪዳን 27፤ ትክክለኛ የእግዚአብሔር ቃል ናቸው በመባል በፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ተቀባይነት አግኝተዋል።

የአዋልድ መጻሕፍት

አስቀድሞ በአይሁድ ዘንድ ስለ መጻሕፍቱ ቁጥር ምንም ጥርጥር አልነበረም። ጌታም ሆነ ሐዋርያት በትምህርታቸው እንዲህ ዐይነት ችግር አላነሱም ነበር። (ማቴ. 21፡42፤ ማር 14፡49፤ ሉቃ. 24፡32፤ ሐሥ. 10፡24፤ 15፡14) እነዚህ መጻሕፍት በጥንቱ የዕብራይስጥ ትርጉም አይገኙም። ነገር ግን ተበታትነው ይኖሩ በነበሩ የግሪክ ተናጋሪ አይሁድ እንደተጻፈ ይገመታል። መጻህፍቱ የተዛባ የታሪክ አቀራረብ የሐሳብ መቃረንም አላቸው። እነዚህን መጻህፍት ዛሬም ቢሆን አይሁድ አይቀበሏቸውም።

እነዚህን መጻሕፍት በ363[1] ዓ.ም. በሎዶቅያ የተደረገው ጉባዔ አውግዞአቸው... አዋልድ (አፖክሪፋ) የተሰወረ ማለት ሲሆን ይህን ስያሜ የሰጣቸው ቅዱስ ጀሮም ነው። ከሌሎች ቅዱሳት መጻህፍት ጋር በአንድ ጥራዝ ዕድል ያገኙትም በ3ኛው ዓ.ዓ. በሴፕቱጀንት እና በ 420 ዓ.ም. (ቩልጋታ) በሚባለው ላቲን ትርጉም ነው። ይሁንና የካቶሊካውያን ጉባኤ በ1546 ትሬንት

[1] በዚህ ጽሑፍ የተጠቀሱት ዓመተ ምሕረቶች በሙሉ እ.አ.አ. ናቸው።

ላይ ባደረገው ስብሰባ ከአዋልድ ሰባቱንና በአሉት ላይ ተጨማሪ ምዕራፎችንና ቁጥሮችን ብቻ ከሌሎች ጋር አንዲቆጠሩ በመወሰኑ በእነሱ ካነን የመጻህፍቱ ቁጥር 73 ነው። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ ሌሎች የኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ከሚቀበሏቸው 79 በላይ ሄኖክና ኩፋሌ የሚባሉትን በመጨመር (በሲኖዶስ ውሳኔ ባይሆንም) የምትገለገልባቸው 81 መጻህፍት ናቸው።

ከካቶሊካዊት ከሌሎች የምስራቅ ጥንታውያን አብያተ ክርስቲያናትና ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን በቀር የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ሰድሳ ሰድስቱን ብቻ ይቀበላሉ። ፕሮቴስታንቶች ከአዋልድ መፃህፍት መካከል አንዳንዶቹ እንደ መልካም ሃይማኖታዊ ሥነ ጽሁፍ ሊቆጠሩ ቢችሉም ከቅዱሳት መጻህፍት እኩል ሊታዩ አይችሉም በማለት አይቀበሏቸውም።

የአዲስ ኪዳን ካነን

የአዲስ ኪዳን መጻህፍት ተጽፈው የወጡት ከ50- 100 ዓ.ም. መካከል እንደሆነ ይታመናል። ሁሉም ተጠቃለው በአንድ ጥራዝ እስኪታወቁ ግን ረዘም ያሉ ዓመታት ወስደባቸዋል።

በሐዋርያት ዘመንና ከእነርሱም በኋላ በነበሩት ጥቂት ትውልዶች ዘንድ ዋና መገልገያ የነበሩት የብሉይ ኪዳን መጻህፍት ብቻ ቢሆኑም የአዲስ ኪዳን መጻህፍትም (1ጢሞ. 5፤18) በመጀመሪያው ሁለት ሶስት መቶ ዓመታት ላይ ትጽፈው የነበሩትና ገና በመጻፍም ላይ የነበሩ መጻህፍት ቁጥር በርካታ ስለነበር ከሁለተኛው መቶ ዓመት ጀምሮ ትክክለኞቹን መጻህፍት ለይቶ የመወሰኑ ተግባር ክርክር እያስነሳ ሄደ። ክርክሩም በየአቅጣጫው እየሰፋ ሳይሰክን እስከ 4ኛው መቶ ዓመት ማብቂያ ድረስ ቆይቶአል።

ከሐዋርያት ዘመን በኋላ በስማቸው እያሌ መጻህፍት ተጽፈው ነበር። ቀደም ሲል የአዲስ ኪዳን መጻህፍት በየአብያተ ክርስቲያኑ እየተነበቡ ይዞሩ ስለነበር፤ ሐሳውያን ትምህርታቸውን ለማስፋፋት እያሌ መጻህፍትን ያወጡ ነበር። ከዚህም የተነሳ የትክክለኞቹን መጻህፍት ዝርዝር ለመወሰን ማከራከሩ አልቀረም። ለመጨረሻ ጊዜ ውሳኔው የጸናው በ325 ዓ.ም. በኒቅያ ጉባዔና በ397 ዓ.ም. በካርቴጅ ጉባዔ ላይ ነው። የካርቴጁ ጉባዔ የመጻህፍቱን አቀማመጥ ቅደም ተከተልም የወሰነ ነው።

ወደ ዕብራውያን ሰዎች፤ የጴጥሮስ የዮሐንስና የይሁዳ መልእክታት በአንዳንድ አገሮች ባለመታወቃቸው የጸሐፊዎቹ ማንነት በውል ባለመታወቁና መልእክታቸው በሌሎች አጠራጣሪ ጽሁፎች (አዋልድ) ውስጥ ተጠቅሰው በመገኘታቸው ጥርጥርና ክርክር በማሥነሳቱ እስከ 220 ዓ፤ም፣ ድረስ በአንዳንዶች ዘንድ ተቀባይነት ሳያገኙ ቆይተው ነበር።

2ኛ ጴጥ. 3፤16 የመሳሰሉት ጥቅሶች እንደሚጠቁሙን የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ከብሉይ ኪዳን መጻህፍት ሥልጣን እኩል መቆጠር የጀመሩት በሐዋርያት ዘመን ጀምሮ ነው። በጥንት የቤተ ክርስቲያን አባቶች ጽሑፎች ትምህርትና በሌሎች ጸሐፊዎች ዘገባ እንደሚታየው ወንጌላትና መልዕክታት ቀደም ሲል ጀምሮ በአብያተ ክርስቲያናት ሕይውት ሥር መስደዳቸውን እንረዳለን። (ቅዱሳት መጻሕፍት) የሚለው ስያሜ ቀድሞ ለብሉይ ኪዳን ብቻ የተሰጠ ነበር። (ሮሜ 1፤2) ከ2ኛው መቶ ዓመት በኋላ ግን የአዲስ ኪዳንም መጠሪያ ሆነ።

የመጻሕፍቱ ካነን እንደተወሰነ (የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ) የሚባለውም ጽሁፍ ወጣ። ጽሁፉ በሐዋርያት ተጽፎ ሳይሆን ትምህርታቸውንና እምነታቸውን የያዘ አስተዋጽዖ ነው

ተብሎ ስለሚታመንና ለአዲስ አማንያን ማስተማሪያ ጠቃሚነት ስላለው በሁሉም ዘንድ ተቀባይነት ሊያገኝ ችሏል።

የምዕራፎችና ቁጥሮች መከፋፈል

ጥንት አይሁድ ለጥናትና ለንባብ በሚያመች ሁኔታ ብሉይ ኪዳንን ይከፋፈሉ ነበር። ቅዱሳት መጻህፍት ሲጻፉ በምዕራፍና በቁጥር የተከፋፈሉ አልነበሩም። ስለሆነም የጥንት አባቶች ይህንኑ ዓላማ የተሳካ ለማድረግ ዛሬ እንደምናየው ለጥናትና ለማስታወስ አመቺ በሆነ መንገድ ከፋፍለው አስተላልፈውልናል።

በምዕራፎች የከፋፈለልን Stephen Langton የተባለ የካንተር በሪ ሊቀ ጳጳስ የነበረ ሰው በ13ኛው ክ.ዘ. ላይ ነው። እንዲሁም Robert Stephanus የተባለ ፈረንሳዊ ሰው በቁጥሮች ከፋፍሎ በ1551 ላይ አሳተመው።**

የጥንት ትርጉሞች

መቼም የመጀመሪያዎቹ የቅዱሳት መጻህፍት ቅጂዎች (ኦሪጅናል) በሙሉ እንደጠፉ የታመነ ነው። ይሁንና ለመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ሥራ መሠረታዊ ማመሳከሪያዎች ናቸው የሚባሉ የጥንት ትርጉሞች በበርካታ ቋንቋዎች ይገኛሉ። (ዕብራይስጥ፤ ግሪክ፤ ላቲን፤ሲሪያክ)

ከእነዚህ ውስጥ ከኦሪጅናል ከሚቀጠሩት ዋና ዋና ጥንታዊ ቅጂዎች የሚከተሉት ይገኛሉ፦

1. ኮዴክስ ሳይናይቲክስ (The Codex Sinaiticus) በ4ኛው መቶ ዓመት እንደተጻፈ የሚታመን፤ በ1933 ዓ፣ም፣ ከራሽያ ተገዝቶ በብሪቲሽ ሙዚየም የሚገኝ (ግሪክኛ) ነው።

2. ኮዴክስ አሌክሳንድሪኑስ (The Codex Alexandrinus) በ5ኛው መቶ ዓመት የተቀዳ ብሪቲሽ ሙዚየም የሚገኝ ግሪክኛ ነው።

3. ኮዴክስ ቫቲካኑስ (The Codex Vaticanus) በቫቲካን ቤተ መጻሕፍት የሚገኝ በ4ኛው መቶ ዓመት የተጻፈ (ግሪክኛ) ነው።

የሙት ባህር ጥቅሎች (The Dead Sea Scrolls)

በ 1947-52 ዓ.ም. ውስጥ ከሙት ባሕር በስተምዕራብ በሚገኝ ምድረ በዳ የኩምራን ዋሻዎች በሚባሉ ሥፍራዎች ውስጥ የተገኙ የዕብራይስጥ እረማይክና ግሪክ ቅጂዎች ናቸው።

እነዚህ ቅጂዎች እስከ ዛሬ ከተገኙ የአርኪዎሎጂ ውጤቶች ከፍተኛ አድናቆት ያተረፉ ናቸው። ምክንያቱም እስከ ዛሬ በሰው እጅ ከሚገኙ የጥንት መጻህፍት ሁሉ የበለጠ ዕድሜ አላቸው;

መጻሕፍቱ መገኘት የጀመሩት በ1947ዓ.ም. በአጋጣሚ ነው። አንድ የዐረብ እረኛ ፍየል ጠፍታበት ሲፈልግ ወደ አንድ ዋሻ ድንጋይ ሲወረውር በድንገት የሸክላ መሰበር ድምጽ ይሰማል። ጓደኛውን ጠርቶ ወደ ዋሻው ሲገቡ በተሰበረው ማሰሮ ውስጥ አያሌ የብራና ጥቅሎች በሐር ጨርቅ ተጠቅልለው ያገኛሉ። (ገንዘብ የሚያስገኝ ነገር ነው) ይሉና ወደ ቤተልሔም ከተማ ወስደው በጭንቅ ለአንድ አቡንና የዩኒቨርሲቲ ፕሮፌሰር በርካሽ ዋጋ ይሸጧቸዋል። በዚያ ወሬ አርኪዮሎጂስቶች ይማረኩና ባደረጉት ፍለጋ በአካባቢው ካሉ ብዙ ዋሻዎች እጅግ በርካታ

ቅጂዎች ተገኝተዋል፤ በተደረገውም ጥናት አካባቢው ታሪካዊ የነበረ የገዳም ሥፍራ መሆኑ ታውቋል።

ኢሴንስ (Essens) የሚባሉ ወግ አጥባቂ የአይሁድ ሃይማኖት ክፍሎች በክርስቶስ ዘመን ነበሩ። (በአዲስ ኪዳን አልተጠቀሱም።) እነዚያ ጥቅሎች የተገኙት በነርሱ ገዳም ነበር። መጻህፍቱም ተገለበጡ የሚባለው በእነርሱ ነው።

የተገኙት መጻሕፍት ከመጽሀፈ አስቴር በቀር የብሉይ ኪዳን ክፍሎች በሙሉና አዋልድ መንፈሳዊ ታሪኮች መዝሙራት ኮሜንታሪዎች ስለ ገዳማቸው የተጻፉ ታሪኮች ወዘተ. ናቸው። ቆይቶም እረኞቹ በጥቂት ብሮች ለእቡኑ የሸጧቸው መጻሕፍት የእሥራኤል መንግሥት በዩኤስ 250,000 ዶላር ገዝቶ (እንደ ታላቅ ቅርስ) አስቀምጧቸዋል። ሌሎች መጻሕፍት በከፊል በዮርዳኖስ መንግሥት እጅ ነበሩ።

የ ል ዩ ል ዩ ት ር ጉ ሞ ች ታ ሪ ክ

1. ግሪክ LXX (ሰባሊቃናት)

የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት መጀመሪያ የተጻፉት በዕብራይስጥ መሆኑ ለሁላችን ግልጽ ነው። ከባቢሎን ምርኮ በኋላ ደግሞ በ6ኛው ዓ.ዓ ላይ አይሁድ ቋንቋቸውን በመርሳታቸው መጀመሪያ በቃል ቆይቶ በስድ ትርጉም (ፓራፍሬዝድ) ሆኖ በአረምኛ ማለትም በአሶራዊያን ቋንቋ እንደተተረጎመላቸው ይተረካል። (1 ነገ 18፡26፤ ነህ 8፡8) አዲስ ኪዳንም በግሪክኛ ቋንቋ ይጻፍ እንጂ አልፎ አልፎ የአረምኛ ቃላት የሚገኙበት ሲሆን ጌታ ኢየሱስም በአርማይክኛ ጭምር እንዳስተማረ ይታመናል። ይሁንና የታወቀው የመጀመሪያው ግሪክኛ ትርጉም ሴፕቱአጀንት (የ70 ሊቃናት ትርጉም) የሚባለው ነው።

በግሪክ የግዛት መስፋፋት ዘመን የግሪክ ባህል ቋንቋና ሥልጣኔ በመስፋፋቱ ተበታትነው ይኖሩ የነበሩ አይሁድ የግሪክኛ ቋንቋ ተናጋሪ ሆነው ስለነበር በአሌክሳንደሪያ የነበሩ የግሪክኛ ተናጋሪ አይሁድ ተረጎሙት የሚል ነው። (አዋልድም ለመጀመሪያ የታከሉት በዚህ ትርጉም ነው)። ይህ ከተተረጎመበት ምክንያት አንዱ ታሪክ ነው፤ በሌላ በኩል ደግሞ በጥሊሞስ ፓቶሎማ ፊላድልፈስ (285-246 ዓ.ዓ) የሚባለው የግብፅ ንጉሥ በአሌክሳንደሪያ ታላቅ ቤተ መጻሕፍት እቋቁሞ ስለነበር ኤሌዘር የተባለውን የአይሁድ ሊቀ ካህን የአይሁድን የሕግ መጻሕፍት (ብሉይ ኪዳንን) እንዲልክለት ስለጠየቀ፣ ሊቀ ካህኑ ከየነገዱ ሰድሰት ሰድሰት በድምሩ 72 ሊቃውንት ይልክለትና በ72 ቀናት ተርጉመው ሴፕቱአጀንት (የሰባ ሊቃውንት ትርጉም) በሚባል የሚታወቀውን ትርጉም ሰጡት ይባላል። ለማንኛውም ትክክለኛው መነሻ አይታወቅም እንጂ ቃሉ በሕዝብ ቋንቋ መተርጉሙ ሕዝቡ ትንቢትን በማንበብ የመሲሑን መምጣት እንዲጠባበቅ ረድቷል።

ከክርስቶስ ትንሣኤ በኋላ ሐዋሪያት አብዛኛውን ለትንቢት ፍጻሜ ማረጋገጫ እየጠቀሱ የሚያስተምሩት ከዚህ ትርጉም ስለነበር አይሁድ አልወደዱትም ነበር። ስለሆነም ከ1ኛው መቶ ዓመት በኋላ አውግዘውታል።

2. ሱሪስት (ሲሪያክ)

ቋንቋው የሶሪያዊያን ሲሆን ይህ ቋንቋ መጀመሪያ ሙሉ መጽሐፍ ቅዱስ ከተተረጎመባቸው የጥንት ቋንቋዎች አንዱ ነው። ምናልባትም በ2ኛው መቶ ዓመት ላይ ነበር። ትርጉሙም በየጊዜው መሻሻል ተደርጎበታል።

3. ላቲን

በሮማዊያን የግዛት መስፋፋት ዘመን ደግሞ ላቲንኛ የተራው ሕዝብ ቋንቋ እየሆነ በመሄዱ ከ3ኛው መቶ ዓመት በኋላ መጽሐፍ ቅዱስን በየግላቸው በላቲንኛ የሚተረጉሙ ግለሰቦች ተነሡ። ይሁንና በግለሰቦች በየግል የተተረጎሙት አስተማማኝ ሆነው ባለመገኘታቸው ፓፓ ደማሡስ የተባሉት የጊዜው የሮማ ቤተክርስትያን ሊቀ ጳጳሳት (366-384 ዓ.ም.) ቅዱስ ጀሮም (Jerome 340-420) ለተባለው ታላቅ ሊቅና መነኩሴ ኃላፊነቱን ሰጥተው ከ22 ዓመታት ሥራ በኋላ በ420 ዓ.ም ተጠናቆ ቩልጋታ የተባለው የሮማይስጥ (ላቲንኛ) ትርጉም ወጣ።

ከዚህም ጋር የአዋልድ መጻሕፍት ቄምር ታክለው ወጥተዋል። ይህ ትርጉም በየዘመኑ መጠነኛ መሻሻል ቢደረግበትም እስከ ዛሬ ድረስ የካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ሕጋዊ መጽሐፍ ቅዱስ ነው ተብሎ ይቆጠራል።

4. ሌሎች

ከ2ኛው መቶ ዓመት በኋላ በሌሎች ቋንቋዎች የመጽሐፍ ቅዱስ የትርጉም ሥራ መስፋፋት ጀመረ። ቅብጥ (ኮፕቲክ)፣ ጎቲክ፣ ጂኦርጂያን፣ ግዕዝ የመሳሰሉት በመጀመሪያዎቹ መቶ ዓመታት ውስጥ ከተተረጎሙት ናቸው። ከዚህም በኋላ አርመንኛ፣ ኑብያን ወዘተ ቀጠሉ።

5. የእንግሊዝኛው መጽሐፍ ቅድስ ትርጉሞች

ወንጌል ወደ እንግሊዝ አገር የገባው በ4ኛው መቶ ዓመታት ውስጥ መሆኑ ቢነገርም በአንዳንድ ግለሰቦች አልፎ አልፎ የቅዱሳት መጻሕፍት ክፍሎች ከመተርጎማቸው በቀር በላቲን ሲነገር ቆይቶ የመጀመሪያው የእንግሊዝኛ ትርጉም የወጣው ጆን ዊክሊፍ (John Wyclif 1329-1384) በተባለ ሰው በ1384 ዓ.ም. ላይ ነው። ይህ ሰው ከሞተ ብዙ ዓመታት በኋላ ትርጉሙና ሥራው ተወግዞ እጥንቱ ከመቃብር ወጥቶ እንዲቃጠል ተፈርዶበታል። (በ1384-ዓ.ም. ሞተ፤ በ1415 ተቃጠለ።)

ዊክሊፍ በትርጉም ሥራው ከመጠላቱ ሌላ ተወግዞ አጽሙ ለመቃጠል የበቃው ምዕመናን ሁሉ የክህነት አገልግሎት መስጠት እንደሚችሉ የክርስቶስ እንጂ የአብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ቃል የበላይነት እንደሌለው ቅዱሳት መጻሕፍት በምዕመናን ዘንድ ሁሉ መዳረስ እንዳለባቸው በመንፈሳዊ ሥልጣን መባለግን በማውገዝ ወዘተ ያስተማራቸው ትምህርቶች ጳጳሳትን በማስቆጣት ነበር። ከዚህም የተነሣ ከኦክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ የማስተማር ሥራው ታግዶ ነበር።

እንዲሁም በፕራግ ዩኒቨርሲቲ ፕሮፌሰር የነበረው ደጋፊውና ተከታዩ ጆን ሑስ (1360-1415) መጽሐፍ ቅዱስን በማሠራጨቱ በቁሙ በእሳት ተቃጥሎ እንዲሞት ተፈርዶበታል። ሆኖም በእነ ጆን ዊክሊፍ ተጀምሮ የነበረው የመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ በመላው አውሮፓ እየተቀጣጠለ ሄዶ ጀርመን አገር ላይ በእነ ሉተር (1483-1546) ጥሩ ውጤት አስገኝቶአል።

ከዚህም በኋላ የፕሮቴስታንት ንቅናቄ የማይገታ ኃይል ሆነ። እርግጥ ነው በሉተርም ዘመን ዊልያም ቲንዴልን (William Tyndale 1494-1536) የመሳሰሉ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስ በመተርጎማቸው ብዙ መከራ ደርሶባቸዋል።

ይህ ሰው ብርቱ የመንፈሳዊ ተሐድሶ መሪና መጽሐፍ ቅዱስ በተራው ሰው ቋንቋ እንዲዳረስ የተጋደለ ሰው ነበር። በአገሩ (በእንግሊዝ) ስደት ስለበዛበት ወደ አውሮጳ ተሻግሮ የበርካታ ቅዱሳት መጻሐፍትን ትርጉም እያጠናቀቀ በማሳተም አሠራጭቷል። በመጨረሻው ተይዞ ከተሰቀለ በኋላ

አስክሬኑ በአሳት ተቃጥሏል። በዚሁ መጠን የእግዚአብሔር ቃል ትርጉም እየተስፋፋ ሄደ፤ የሚከተሉትም የእንግሊዘኛ ታዋቂ ትርጉሞችም ወጡ-

ኪንግ ጀምስ ትርጉም (King James Version) በ1611 ዓ.ም. 47 በሚሆኑ ምሑራን የተተረጎመ ነው። በከፍተኛ ጥንቃቄ የተሠራ በመሆኑ አስከ ዛሬ በመላው ዓለም የሚሠራበት ነው።

አር. ኤስ. ቪ (RSV)
ቲኢቪ ትርጉም (TEV) በ1976 ዓ.ም በዛሬው እንግሊዘኛ የተተረጎመ።
ጀሩሳሌም ባይብል (Jerusalem Bible) በ1966 ዓ.ም. በካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ምሑራን የተዘጋጀ ዘመናዊ ትርጉም ሲሆን ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን የምትቀበላቸውን የአዋልድ መጻሕፍት ጭምር ይዟል።

ኤን. አይ. ቪ (NIV) በ1979 ዓ.ም ትርጉሙ ከ10 ዓመት በላይ ፈጅቷል ተርጓሚዎቹ ከልዩ ልዩ ሙያ የተወጣጡ ከ100 በላይ ግለሰቦች ነበሩ።

6. የሚሲዮናውያን እንቅስቃሴ

የተጀመረው ከ16ኛው መቶ ዓመት ወዲህ ቢሆንም በተለይ ከ18ኛው መቶ ዓመት ጀምሮ የአውሮፓ ቅኝ ገዥዎች ግዛታቸውን ለማስፋፋት በአራቱ ማዕዘናት ሲዘምቱ፤ ሚሲዮናውያንም አጋጣሚውን ተጠቀሙበት። እነሱም በየሄዱባቸው አህጉራት ፣ መጀመሪአ ለቋንቋዎች ፊደላት በማበጀትና ሰዋስው በመሥራት በብዙ መቶ ልሳናት ቃሉን ለመተርጎም በቅተዋል።

7. የመጽሐፍ ቅዱስ ማሕበራት እንቅስቃሴ መጀመር

ከ19ኛው ምዕተ ዓመት መግቢያ ወዲህ መጽሐፍ ቅዱስ በመተርጎምና በማሰራጨት ከፍተኛውን ምዕራፍ የያዙት መጽሐፍ ቅዱስ ማሕበራት ናቸው።
መጀመሪያ የተመሰረተው የመጽሐፍ ቅዱስ ማሕበር (የእንግሊዝና የውጭ ሀገሮች የመጽሕፍ ቅዱስ ማሕበር) የሚባለው ለንደን ላይ ሲሆን ዘመኑም 1804 ዓ.ም.ነበር። በዚያን ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስ የተተረጎመባቸው የዓለም ቋንቋዎችም 72 ያህል ብቻ ነበሩ።

በአሁኑ ጊዜ አብዛኛውን የቅዱሳት መጻሕፍት ትርጉም የሚካሄደው በነዚህ ማህበራትና የአብያተ ክርስቲያን ትብብር ነው። ቅዱሳት መጽሕፍት የተተረጎመባቸው የዓለም ቋንቋዎችም ከ1850 በላይ ደርሷል።

የእንግሊዙ ማኅበር በሀገራችን ቋንቋዎች ቅዱሳት መጻሕፍትን በማተምና በማሰራጨት ለብዙ ዓመታት አገልግሏል። ከ1914 ዓ.ም. ጀምሮም አዲስ አበባ ላይ በኦፊስል ወኪል ቤት በሚቋቋም ሕንፃ በመሥራትና ቤቱን በማጠናከር አገልግሎት ሰጥቶአል። ከ1972 ዓ.ም. ወዲህ ግን ማህበሩ {የኢትዮጲያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር} በሚል ስም ራሱን ችሎ ብሔራዊ ማኅበር ሆኗል። ማኅበሩም የሚመራው ከተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት በተመረጡ የቦርድ አባላት ነው። ይህ ብሄራዊ ማኅበር በአሁኑ ጊዜ ከአብያተ ክርስቲያናት ጋር በመተባበር ከ 20 በበለጡ የሃገራችን የብሄረሰብ ቋንቋዎች ቅዱሳት መጻሕፍትን በመተርጎም በማሳተምና በማሰራጨት ምዕመናንን ያገለግላል።**

ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ተርጓሚ ማኅበራት

በአሁኑ ጊዜ ከመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበራት ሌላ ሌሎች በርካታ የመጽሐፍ ቅዱስ ተርጓሚ ማኅበራት ይገኛሉ። ከእነዚህም መካከል ዊክሊፍ የመ.ቅ. ተርጓሚዎች {WBT} የተባለው አንጋፋ ድርጅት ይገኝበታል።

የጎትመት መሣሪያ የሰጠው አስተዋፅኦ

ከቅዱሳት መፃህፍት የትርጉም ዕድገት ጋር ሳይጠቀስ የማይታለፍ ሌላ ቁም ነገር አለ። ይኸውም፤ የተተረጎሙት መጻሕፍት ባጭር ጊዜና በርካሽ ዋጋ በብዛት ለመስራጨት ያበቃቸው በ15ኛው መቶ ዓመት የጎትመት መሣሪያ መፈልሰፍ ጉዳይ ነው። ከዚያ ዘመን በፊት መፃሕፍቱ ቢተረጎሙም እንኳ በእጅ እየተገለበጡ መዳረስ ስለነበረባቸው ባጭር ጊዜና ሕዝብ ሊገዛ በሚችልበት ዋጋ ሊዳረሱ አይችሉም ነበር። በ1456 ዓ.ም. ጀርመን ሀገር ላይ የማተሚያ መሣሪያ ሲሠራ ለመጀመሪያ ጊዜ በጎትመት የወጣ (የጉተንበርግ መጽሐፍ ቅዱስ) በመባል የሚታወቀው ላቲንኛ ወይም ቮልጌት የተባለው ነበር።

የቅዱሳት መጻሕፍት ትርጉም በሀገራችን ቋንቋዎች

1. ግዕዝ

የእግዚአብሔር ቃል ቀደም ሲል ከተተረጎመባቸው ጥንታዊያን የዓለም ቋንቋዎች አንዱ ግዕዝ ነው። ይህም የእግዚአብሔር ቃል በቋንቋቸው አስቀድሞ ካገኙት ሀገሮች ኢትዮጲያ አንዷ ነች ማለት ነው።

ለመሆኑ ይህ ትርጉም እንዴት፣ መቼ፣ በማንስ ተተረጎመ? ታሪኩ ከታወቀው የወንጌል መልዕክተኛ ቅዱስ ፍሬምናጦስ ይጀምራል።

አድስዩስ የተባለ የግሪክ ነጋዴ ከጢሮስ መሮጵዩስ ከፊንቄ (ሐሥ 21:3-7) ሕንድን ለመጎብኘት እንደኛው ፍሬምናጦስ ሁለት ወጣት ዘመዶቹን አስከትሎ በመርከብ ሲጓዝ ኤርትራ ባሕር ወደብ ላይ ሰንቅ ፍለጋ እንዳረፉ እሱንና ሌሎችን የአካባቢው ነዋሪ ደርሶ ይገድላቸዋል። ሁለቱ ወጣቶች ወደ ንጉሡ ይወሰዳሉ። ንጉሡም ንቃታቸውን አይቶ አንዱን ጠጅ አሳላፊው ፍሬምናጦስን ጸሐፊው ያደርገዋል። ቆይቶ ንጉሡ ሲሞት ወደ ሀገራቸው የመመለስ መብት ቢሰጣቸውም ንግሥቲቱ አልጋ ወራሹ አስኪያድግ እንዲረዷት ስለለመነቻቸው ፍሬምናጦስ ይቀራል።

ወንጌልንም የማስተማር ኃላፊነት የሰማውና ይጀምራል። አልጋ ወራሹን ሌሎችንም ወደ እምነት ይመራል። በመጨረሻም ወደ አሌክሳንደሪያ ሄዶ ለአቡኑ ለአትናቴዎስ ሁኔታውን ያሰረዳና አቡን እንዲልክ ሲጠይቀው "ካንተ የተሻለ ለአቡንነት የሚበቃ የለም" በማለት ባርኮ ይልከዋል። (ከዚያ ወዲህ የኢትዮጲያ ቤተ ክርስቲያን አቡን ከአሌክሳንደሪያ በመላክ እስከ 1956 ቆይቷል።) ይህ ሰው አባ ሰላማና ከሳቴ ብርሃን በሚሉት ስሞች በሀገራችን ይታወቃል።

አባ ሰላማ ቅዱሳት መጻሕፍት ወደ ግዕዝ አልፎ አልፎ እንደተረጎመ ቢጠቀስም በዚህ ረገድ ታዋቂዎቹ ተሰዓቱ (ዘጠኙ) ቅዱሳን የሚባሉት ናቸው። እነዚህ ሰዎች ከልዩ ልዩ ሀገር በደረሰባቸው የሃይማኖት ስደት ምክንያት የመጡ ነበሩ። (ከሶርያ ቁስጥንጥንያ ወዘተ) ተሳቱ ቅዱሳን ወደ ኢትዮጵያ መጡ የሚባለው በ499 ዓ.ም. ላይ ሲሆን፤ ወደ ኢትዮጲያም እንደደረሱ ቀደም ሲል በፍሬምናጦስ የክርስትናን እምነት ተቀብሎ የነበረው የአክሱም መንግሥት የሞቀ መስተንግዶ በማድረግ እንደተቀበላቸው ይገመታል። (እንዳንድ ታሪኮች እንደሚጠቁሙት ወንጌላት አባ ሰላማ

እንደተተረጎሙ ስለሚገልጹ የአክሱም ዘመን መንግሥት በሥነ ጽሑፍ የዳበረ እንደነበር ይገመታል።)

ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ ገባ የሚባለው በሐዋሪያት ዘመን እንደሆነ ይተረካል። 1ኛው ግምት በሐዋሪያት ሥራ በተጠቀሰው ጀንደረባ ሲሆን 2ኛው "ከሐዋሪያት አንዱ ቅዱስ ማቴዎስ ወንጌልን ሲሰብክ ሰማዕት የሆነው በኢትዮጵያ ነው" የሚባለው ነው። እንዲሁም የንግሥተ ሳባን (ንግሥት አዜብ) ጉብኝት በማስመልከት በሚነገረው ታሪክ (ክብረ ነገሥት) ከሰሎሞን ምኒልክ የሚባል ልጅ እንደተወለደ ባደገ ጊዜ አባቱን ጉብኝቶ ሲመለስ ሌዋዊያን ብሉያትንና ታቦት ይዘው በመምጣት ማስተማር እንደጀመሩ ይነገራል። ይሁንና በ4ኛው መቶ ዓመት ላይ የአክሱም መንግሥት በንጉስ ኢዛና አብርሃ በኦፊሲየል ክርስትናን እስከተቀበለ ድረስ የተገኘው ቅርስ የለየለት ጣዖት አምላኪ አረማዊ ሕዝብ እንደነበር ተገልጿል።

ተሰዓቱ ቅዱሳን መጀመሪያ ግብጽ ወርደው የብህትውናን ኑሮ በማጥናት ወደ ኢትዮጵያ ይገባሉ። አክሱም ጥሩ አቀባበል ያደርግላቸውና የግዕዝን ቋንቋና የሕዝቡን ባህል በማጥናት በልዩ ልዩ አቅጣጫ ተሰማርተው ወንጌልን እያስተማሩ ገዳማትንና የገዳምን ኑሮ ሥርዓት መሠረቱ። አብያተ ክርስቲያናትን ተከሉ። በመጨረሻም የእግዚአብሔርን ቃል ትርጉም ከፍጻሜ በማድረስ የጌታን ቃል ከረዥም ዓመታት በፊት በቋንቋቸው ካገኙት አገሮች አንዷ እንድትሆን በመጣር ለኢትዮጵያ ታላቅ ቅርስ ትተው አልፈዋል። የተረጎሙት ምናልባት በየግል ይሆናል ምክንያቱም የግዕዙ ትርጉም ፈሊጥ በጣም የተለያየና ትርጉሙም ብዙ ስሕተት ይገኝበታል ስለሚባል ነው። እነርሱ የተረጎሙት መጽሐፍ ቅዱስ በ14ኛው መቶ ዓመት ላይ መሻሻል ሳይደረግበት አልቀረም።

2. የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ

የመጀመሪያው የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ተርጓሚ አባ ሮሜ ይባላል። ይህ ሰው ትክክለኛ ኢትዮጵያዊ ስሙ አባ አብርሃም እንደሆነ ይገመታል። የተማረ የቋንቋ ሊቅና መነኩሴ የነበረ የጎጃም ተወላጅ ነበር። ዕድገቱና ትምህርቱ ግን በጎንደር ዙሪያ ነበር።

አባ ሮሜ በ29 ዓመቱ በምድረ ግብፅ አቋርጠ ኢየሩሳሌም እንደሄደ በዚያውም ወደ ሶሪያ አርሜንያ ፐርሺያና ሕንድ ድረስ በንግድ ሲዘዋወር እንደቆየ ይነገራል።

ከእነዚህ ሀገሮች ጉብኝቱ በኋላ ወደ ሀገሩ ተመልሶ ጥቂት ከቆየ በኋላ ወደ ካይሮ እንደገና ይሄዳል። በዚህ ጊዜ ዕድሜው ከ50 ሳያልፍ አይቀርም። አባ ሮሜ ካይሮ ሳለ በጠና ታሞ በሞት አፋፍ ላይ ሳለ በግብፅ የፈርንሳይ ምክትል ቆንሲል የነበረ አሰሊን የሚባል ሰው አስታሞ ያድነዋል።

በዚህ ትውውቅ አሰሊን የአባ ሮሜን የሥነ ጽሑፍ ዕውቀትና የቋንቋ ችሎታውን በመገንዘብ (የፋርስ፣ የጣሊያንኛ፣ የግሪክኛ፣ የዐረብኛና የሌሎችም ቋንቋዎች ችሎታ ነበረው) መጽሐፍ ቅዱስን ወደ አማርኛ እንዲተረጉም ያበረታታዋል። አባ ሮሜ ይህን ታላቅ አደራ በመቀበል አሰሊን አስቸጋሪ ቃላትን በማብራራትና አስፈላጊ መረጃዎችን በማቅረብ እየረዳው የትርጉሙን ሥራ በ10 ዓመታት ውስጥ (1808-1818) ለማጠናቀቅ በቃ።

አባ ሮሜ ትርጉሙን እንደጠናቀቀ ኢየሩሳሌምን በድጋሚ ለመጎብኘት በነበረው ጉጉት መሠረት ወደዚያው ተጓዘ። ነገር ግን የሥራ ፍሬውን በጎተመት ላይ ውሎ ሳያይ በ1819 ዓ.ም. ወደ ግብፅ እንደተመለሰ ካይሮ ላይ ዐረፈ።

በሌላ በኩል የእንግሊዝ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር በኢትዮጵያ የብሔረ ሰብ ቋንቋዎች የእግዚአብሔርን ቃል አትሞ ለማቅረብ ፍለጋ ያደርግ ነበር። በታህሣሥ 1818 ዓ.ም. ጁዌት (W. Joweet) የተባለ በሚድትራኒያን የChurch Missionary Society ወኪል ወደ ግብፅ እንደሄደ ከአሰሊን ጋር ይገናኛሉ። በዚያ ግኙኝነት ጁዌት የአማርኛውን ትርጉም ቅጂ ከአሰሊን ላይ በ1250 የእንግሊዝ ፓውንድ ገዝቶ ለእንግሊዝ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ያስረክባል። ማኅበሩ የትርጉሙን ጥራት አስመርምሮ ወንጌላትን በ1824 ዓ.ም. አዲስ ኪዳንን በ1829 ዓ.ም. ሙሉውን መጽሐፍ ቅዱስ በ1840 ዓ.ም. ለንደን ላይ አትሞ ወደ ሀገራችን በመላክ ማሠራጨት ጀመረ።

የአባ ሮሜን ትርጉም ማርቲን ፍላድ የተባለ እንግሊዛዊ ሚስዮናዊ ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ጋር ካረመው በኋላ በ1878 ዓ.ም. እንደገና ታትሟል። ዮሐንስ ክራፐፍ የተባለው ሚስዮናዊም ከዕብራይስጥ ጋር የማስማሚያ ርማቶች አድርጎበታል።

የ1962 ዓ.ም. ትርጉም

ይህ ትርጉም በአሁኑ ጊዜ በዋና ሥርጭት ላይ የሚገኘው ነው። ትርጉሙ የተዘጋጀው በኢትዮጵያውያንና በሚስዮናውያን ትብብር በቀድሞው ንጉሥ ኃይለ ሥላሴ ትእዛዝ የተተረጎመ ነበር። ነገር ግን ይህም ደግሞ ለአዲሱ ትውልድ አማርኛው ከባድ እየሆነ በመሄዱ በቅርቡ ትርጉሙ ተጠናቆ ለኅትመት የቀረበ የዛሬው አማርኛ ትርጉም ተዘጋጅቷል። የዚህ ትርጉም አካል የሆነው አዲስ ኪዳን በኢትዮጵያ አቆጣጠር ከ 1973 ዓ.ም. ጀምሮ በሥርጭት ላይ ይገኛል።

3. ትግሪኛ

የትርጉሙ እንቅስቃሴ ከአያሌ ዓመታት በፊት ጀምሮ የነበረ ቢሆንም የብሉይ ኪዳን ትርጉም በየምክንያቶች ሳይጠናቀቅ ኖሮ በቁስ አምባዬ ሀብተእግዚና በእንዲት የሰዊድን ሚስዮናዊት ተጠናቆ የታተመው በ1956 ነው። ቀደም ሲል የትግሪኛ መማሪያ በ1890 የመዝሙር መጽሐፍና አራቱ ወንጌላት ታተሙ በ1909 አዲስ ኪዳን ታተመ። እንዲሁም ቁስ ተወልደመድኅን የተባሉት ሰው ከመጀመሪያዎቹ ተርጓሚዎች መካከል ከፍተኛ አስተዋጽዎ ያደረጉ ሰው ነበሩ።

ከ1894 ዓ.ም. በፊት የንባብ መማሪያ፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክና ከዘፍጥረት እስከ ሣሙኤል ያሉት መጻሕፍት ገበረ ኢዎታቲዎስ በተባለ ሰው ተተርጉመው ነበር። (ይህ ሰው በኋላ ወደ ወለጋ ሄደው ወንጌልን ካስፋፉ ሰዎች አንዱና ዋናው ነው።)

አዲስ ክለሳ በአሁኑ ጊዜ በመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር አማካይነት ከኦርቶዶክስ፣ ካካቶሊክና ከፕሮቴስታንት አብያተ ክርስትያናት የተወከሉ ተርጓሚዎች የክለሳ ትርጉም እየሠሩ ነው።

4. ኦሮምኛ

ከኦናሲሞስ በፊት ዶር. ክራፐፍና ዘነበ በተባለ የአጼ ቴዎድሮስ ጸሐፊ (1870-77) የተተረጎመው የኦሮምኛ ቅዱሳት መጻሐፍት እንደነበሩ ይነገራል። ክራፐፍ በአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ ላይም አርማት ያደረገ የጀርመን ሚሲዮናዊ ነበር።

ኦነሲሞስ የመጀመሪያው ስሙ "ሐይካ" ሲሆን ፍቺው ባጋጣሚ ተርጓሚ ማለት ነው። ኦነሲሞስ (1856-1931) በኢሉባቦር ክፍለ ሀገር ተወልዶ በአራት ዓመቱ አባቱ ሞተበት።

ብዙ ሳይቆይ ባሪያ ፈንጋዮች ከእናቱ ሰርቀው ይሸጡትና ስሙ ነሲብ ተባለ። ቀጥሎ በሌሎች ባሪያ ፈንጋዮች ተሰርቆ ተሸጠ።

በዚህ ሁኔታ ለአራት ጊዜ ተሸጠዋል። በመጨረሻም በ1870 ላይ ባንድ ሚሲዮናዊ ነፃ ወጥቶ ሎሌው ይሆናል። በ1872 ላይ በ16 ዓመቱ "ኦነሲሞስ" በሚል የክርስትና ስም ይጠመቃል። ከ1876-1881 ስዊድን ሀገር ቆይቷል። ኦነሲሞስ አስቀድሞ የሉተርን ካታኪዝም፣ የሰው ልብ፣ መዝሙራትና ሌሎች መጻሕፍትን ተርጉሟል። ቀጥሎ አስቴር ጋኖ ከተባለች ረዳት ጋር በብዙ ጥረት የተረጎመው አዲስ ኪዳን በ1893 በአምኩሉ ማተሚያ ቤተ ታተመ።

ብሉይ ኪዳንን በስኔ ወር 1897 አጠናቀቀ። በኋላ በስኔ 1899 በራሱ በኦነሲሞስ ተቆጣጣሪነት በቅዱስ ክሪሽና ማ/ቤት ታተመ።

አዲሱ ትርጉም በዛሬው ጊዜ የኦሮምኛ መጽሐፍ ቅዱስ በዘመናዊ ኦሮምኛ አንደገና ተተርጉሞ ለጎትመት እየተዘጋጀ ነው። አዲስ ኪዳን ግን ቀደም ሲል ታትሞ በሥርጭት ላይ ይገኛል።

5. ለሎች

ቀደም ባሉት ዘመናት በትግረ በአኝዋክኛ በኑኤርኛ በኩናምኛ ቋንቋዎች አዲስ ኪዳኖች ተተርጉመው ታትመዋል። በሌሎች በርካታ የብሔረሰብ ቋንቋዎች ደግሞ ልዩ ልዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ተተርጉመው ታትመዋል።

ባሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበርና በአብያተ ክርስቲያናት ጥረት ከሃያ በበለጠ የሀገራችን የብሔረሰብ ቋንቋዎች ቅዱሳት መጻሕፍት በመተርጎም ላይ ይገኛሉ። ከእነዚህም ውስጥ ጅህኛ፣ ከምባትኛ፣ ሃድይኛ፣ ጌዲኦኛ፣ ወላይትኛ፣ ጊሚርኛ፣ ሲዳምኛ፣ አኝዋክኛ፣ ቡርጅኛ፣ ከፍኛ፣ ኮንሶኛ፣ አፋርኛ . . . የመሳሰሉት ይገኙባቸዋል። ከእነዚህም ውስጥ ወላይትኛ፣ ጌዲኦኛና ጅህኛ አዲስ ኪዳኖች ታትመዋል።

በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የደረሱ ስደቶች

በመሠረቱ ቤተ ክርስቲያን ከተመሠረተችበት ጊዜ ጀምሮ ከስደት አላረፈችም። ሐዋርያትም ዘመናቸውን ያሳለፉት በስደት ነው። እንዲሁም የእውነተኛ አማኞች ትውልድ ሁሉ ሲሰደድ ቆይተዋል።

የ20ኛው መቶ ዓመት ስደት ካለፉት ዘመናት ስደት ጋር ሲነጻጸር ዝቅተኛ ይመስላል። እርግጥ ነው በ4ኛው መቶ ዓመት ላይ በቆስጠንጢኖስ ወደ ክርስቲያና መለወጥ ለቤተ ክርስቲያን ነጻነት ከታወጀበት ጊዜ ጀምሮ ሕጋዊ አብያተ ክርስቲያናት በመፈጠራቸው ስደቱ የተለያየ መልክ ይዟል።

ተሳዳጁ ሕጋዊት ቤተ ክርስቲያን ከዓለም ኃይሎች ጋር ተባብራ አሳዳጅ መሆኗ አስደናቂው ታሪክ ነው። በራሷ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን በመንግሥትም ጉዳይ ባለሥልጣን በመሆን ይልቁንም ተልእኮዋን ረስታ ወግና ባህልን ማጥበቅ ያዘች። የእግዚአብሔር ቃል ወደ ሰዎች እጅ እንዳይገባ በሲኖዶሷ ማገድ ጀመረች። (በ1229 ሲኖድ ኦፍ ቶውሎስ [Synod of Toulouse] በሚባለው መጽሐፍ ቅዱስ ይዞ የተገኘ ፍርዱ "በእሳት ተቃጥሎ" እንዲሞት ነበር።

ቅዱስ መጽሐፍ ወደ ተራው ሰው እጅ እንዲገባ የሚታገሉትንም ሁሉ ማውገዝ ማሰር መግረፍ ማሳደድ ባኋላ እደረገችው።

በኋላ መንፈሳዊ መነቃቃት እያየለ በመሄዱ ልትቆጣጠረው እንዳልቻለች ስትገነዘብ ሕጉን አሻሻልን በማለት "ማንም ሰው ግለሰቡ መጽሐፍ ቅዱስን ለማንበብ ብቁ ነው ብሎ ጳጳሱ የምስክር ወረቀት ካልሰጠው በቀር መጽሐፍ ቅዱስ ይዞ ቢገኝ ውግዝ ነው" ተባለ።

ተራው ሰው እንዳያነብ ይቀርቡ ከነበሩት ምክንያቶች
1. ምዕመናኑ ያላስተማሪ ቢያነቡት አይረዱትም
2. የቤተ ክርስቲያንን ጎብረት ያፋልሳል
3. ክህደትን ያስከትላል የሚሉ ነበሩ።
እነዚህ ጥንታዊያን አብያተ ክርስቲያናት መጽሐፍ ቅዱስን እስከ ዛሬ ለምን ሲያሳድዱ እንደኖሩ ለመገንዘብ ያዳግታል።

ዛሬ በኢአማንያን እንደሚደረግ የምንሰማውን የቅዱስ መጽሐፍ ማቃጠል ማሳደድ እነርሱም ሲፈጽሙት ኖረዋል።

በዚህ ዓይነት መጽሐፍ ቅዱስ የታቦት ያህል እንዲከበር እንጂ እንዳይነካ፣ ቅድስናው ተጠብቆና ተከብሮ እንዲኖር በጥንታዊው ቋንቋ ብቻ "በመቅደስ ውስጥ ብቻ በካህናት መነገር አለበት" በማለት አፍነውት ኖረዋል። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጸሐፍትንና ፈሪሳዊያንን ከእምነት ይልቅ ወግና ሥራዓትን በማጥበቃቸው እንደወቀሰ እነዚህንም እንደሚወቅስ አያጠራጥርም። (ኢሳ 29፡13-15፤ ማቴ 23፡13)

ዘላለማዊ መጽሐፍ
መጽሐፍ ቅዱስ "የተዓምር መጽሐፍ" ይባላል። ይህ ቅጽል የተሰጠው ግን ስለ አስደናቂ ነገሮች ስለሚተርክ አይደለም። በየዘመኑ በተነሡበት ጠላቶች ላይ እያሸነፈ ሲሰራጭ በመኖሩ እንጂ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ በዓለም ዙሪያ ጦርነት የታወጀበት የተሰደደ እንዳይተረጉም እንዳይታተም እንዳይሰራጭ የተወገዘ የለም። እየተሰበሰበ ተቃጥሏል። ዳሩ ግን ከዓመት ዓመት ቤስት ሴለር (ከፍተኛ ገበያ ያለው) ነው። ለምን ግን ሊጠፋ አልቻለም?

መዝ 119፡89፤ ኢሳ 40፡8፤ ማቴ 24፡35፤ 1 ጴጥ 1፡25 በመመልከት መረዳት ይቻላል። መጽሐፍ ቅዱስን መሪዎች፣ ጠበብት፣ ፈላስፎችና ተራው ሰው "ታላቁ መጽሐፍ" ይሉታል። ይህ መጽሐፍ በየዓመቱ በሚሊዮን ወደሚቆጠሩ ቤቶች ይገባል። ይህ መጽሐፍ "እኔ ማነኝ? ለምን ተወለድሁ? አምላኬን እንዴት ማወቅና ማስደሰት እችላለሁ?" የሚሉ የሰው ልጆችን መሠረታዊ ጥያቄዎች ይመልሳል። መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ከዓለሙና ከሰው ጋር ያለውን ግኑኝነት እንዲሁም ሰው ከሰው ጋር ሊኖረው የሚገባውን ግኑኝነት ይገልጻል። የደኅንነትን መንገድ፣ የዕረፍትና የሰላምን መንገድ ግልጽ ባለ ሁኔታ ያመለክታል። የእልፍ አእላፋት እንባቢዎችን ሕይወት ይለውጣል። የብዙዎችንም ሕይወት ያጽናናል፤ ይመራል፤ ያበረታታል፤ የኅብረተሰብን ኑሮ ለውጧል። (ኤር 23፡29፤ ሮሜ 1፡16)።

"የእግዚአብሔርን ቃል እንደ መንፍስ ቅዱስ ሰይፍ ያዙ።" ኤፌ 6፡17